# የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁና ሸፍጠኛ ዓላማው!!!

አገዛዙ መጠነ ሰፊ የፀረ ሕዝብ ዘመቻ ለማድረግ በመዘጋጀቱ ነው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አስቀድሞ ያወጀው፡፡ እንዴት ለምን የሚሉ ነገሮችን በዝርዝር እናያላን!!!

ትናንትና እንደሰማቹህት አገዛዙ ለአምስት ወራት የሚቆይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጇል፡፡ ሰዉ የታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከኮሮና ቫይረስ ጋራ የተያያዘ መስሎታል፡፡ ነገር ግን አይደለም፡፡ አገዛዙም "የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በምን በምን ጉዳይ ላይ ያተኮረ እንደሆነ በየጊዜው በሚወጡ ዝርዝር መግለጫዎች ይገለጣል!" አለ እንጅ ከኮሮና ቫይረስ ጋር በተገናኘ መሆኑን አልገለጠም!!!

ይሄ በኮሮና ቫይረስ ሳቢያ የተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ለዚህ አገዛዝ ያልታሰበ ሲሳይ አምጥቶለታል ወይም ፈጥሮለታል፡፡ ሁለት ዋና ዋና ነጥቦችን ብቻ እናነሣለን፦

1ኛው. አገዛዙ በኮሮና ቫይረስ አሳቦ ምርጫን አራዝሟል ወይም የሚራዘምበትን ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ አልገባንም እንጅ አገዛዙ ወትሮውንም ቢሆን ምርጫው ዘንድሮ እንዲደረግ አልፈለገም ወይም አልፈቀደም ነበር፡፡ ምርጫውን በአየር ንብረቱ አመሃኝቶ ለማራዘም እንዲመቸውም ነበር የትም ሀገር ምርጫ ተደርጎ በማያውቅበትና ለምርጫ ፈጽሞ በማያመቸው የክረምት ወር ላይ ገፍቶ ወስዶት የነበረው!!!

የክረምት ወቅት የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ዋጋ ቢስ ለማድረግ ያሰበ አገዛዝ ካልሆነ በስተቀር ዘንድሮ የሀገር አቀፍ ምርጫ እንደሚደረግ ከዓመታት በፊት ጀምሮ እየታወቀ አገዛዙ ከቅጥረኛው የምርጫ ቦርድ ጋር ለተንኮሉ ሆን ብሎ ተኝቶ ከከረመ በኋላ አሁን መጨረሻ ላይ ጊዜ ያጠረው መስሎ በመቅረብ ቀድሞ ምርጫ ይደረግ ከነበረበት የግንቦት ወር አንሥቶ በድቅድቁ የክረምት ጨለማ ወቅት ነሐሴ ላይ አደረገው፡፡ ክረምት በወረቀት ለሚደረግ ምርጫ አይደለም ኤሌክትሮኒክ ለሆነ የሠለጠነው ዓለም ምርጫ እንኳ ፈጽሞ የማይመችና ተመርጦም የማያውቅ ወቅት ነው!!!

አገዛዙ ምርጫው ክረምት ላይ የሚደረግ አስመስሎ ከቆየና በምርጫው ሰበብ ሀገሪቱን ላላስፈላጊ ወጭና ኪሳራ ከዳረገ በኋላ መጨረሻ ላይ ምርጫውን ለማራዘም ሊሰጥ የነበረው ምክንያት "80% የሀገሪቱ ሕዝብ በሚኖርበት ወደ ገጠር ምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ መስጫ ወረቀቶችንና ተያያዥ ሰነዶችን በእንስሳት በማጓጓዝ ሒደት በዝናብ ከአገልግሎት ውጭ የሆነበት ወይም የተበላሸበት አደጋ በሰፊው ስላጋጠመና የገጠር የድንኳን የምርጫ ማስፈጸሚያ ጣቢያዎችም ሁኔታ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ከክረምቱ ዝናብ መከላከል የሚችሉ ባለመሆናቸው በዚህ ሁኔታም ምርጫ ማኪያሔድ የማይታሰብ ሆኖ ስለተገኘ!" የሚል ምክንያት በመጨረሻ ሰዓት ላይ በመስጠት ምርጫውን ለማራዘም ነበር አስቦ የነበረው፡፡ ይሁንና ያልታሰበው የአገዛዙ ሲሳይ ኮሮና ቫይረስ መጣና ከዚህ ሁሉ ጣጣ ገላገለው!!!

አገዛዙ የኮሮና ቫይረስ የሚያስከትለው አደጋ ምን እንደሆነ ገና ባልታወቀበት ሁኔታ ቸኩሎ ቅጥረኛው የምርጫ ቦርድ ወጥቶ "ወረርሽኙ ባሳደረው ተጽእኖ ምክንያት ዘንድሮ ምርጫ ላኪያሕድ አልችልም!" የሚል መግለጫ እንዲሰጥ አደረገ፡፡ አገዛዙ ቸኩሎ በአሁኑ ጊዜ ቅጥረኛውን የምርጫ ቦርድ ይሄንን መግለጫ እንዲሰጥ ያደረገበት ምክንያት ወረርሽኙ የታሰበውን ወይም የተፈራውን ያህል አደጋ ሳያደርስ የሚቀርና

የሚከስም ከሆነ ምርጫው ሊደረግ የሚችልበትን ዕድል ስለሚያሰፋ ከወዲሁ ቅጥረኛው የምርጫ ቦርድ ዘንድሮ ምርጫ እንደማያደርግ አስቦ ዝግጅቱን እንዲገታ በማድረግና መስተጓጎሎች እንዲፈጠሩ በማድረግ በኋላ ላይ ወረርሽኙ ቢከስምና የተፈራው ሁሉ ነገር ሳይደርስ ቢቀርና ምርጫ ማድረግ የሚቻልበት ዕድል ቢኖርም እንኳ ምርጫ ቦርድ አስቀድሞ ምርጫ ማድረግ እንደማይችል በማሰቡና በመወሰኑ ምክንያት የተፈጠሩ መስተጓጎሎች ምርጫ ለማድረግ እንዳይችል ስለሚያደርገው ይሄንን አጋጣሚ ፈጥሮ ምርጫ ለማራዘም እንዲመች ነው ቸኩሎ አሁን የምርጫ ቦርድ "አልችልም!" እንዲል ያደረገው!!!

አሁን ደግሞ አገዛዙ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ይሄ ሽፍጡ መጨረሻ ላይ ሳይገባቸው አይቀርምና በገባቸው ጊዜ ደግሞ ችግር እንደሚፈጥሩ ወይም አለመረጋጋት እንዲከሰት እንደሚያደርጉ ስለገባው የፓርላማው የሥልጣን ዘመን ሳይጠናቀቅ አስቀድሞ ትናንትና ለአምስት ወራት የሚቆይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከዚያም በኋላ ሁኔታው እየታየ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ማራዘም የሚቻልበትን ዕድል ክፍት በማድረግ የአስቸኳይ ጊዜ አውጇል!!!

ምክንያቱም የምርጫው መራዘም ብዙ ጎትቶ የሚያመጣው ችግር አለና ነው፡፡ የሽግግር መንግሥት ሕጋዊ ጥያቄ አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ዘንድሮ አገዛዙ ኮሮጆ ገልብጦ "100% አሸነፍኩ!" ብሎ "አገኘሁት!" ያለው የመንግሥትነት የሥልጣን ዘመን ስለሚጠናቀቅ ወይም ሥልጣን ስለማይኖረውና ከዚያ በኋላ ያለ ባለድርሻ አካላት ማለትም ያለ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማኅበራትና ሕዝቡ ፈቃድ፣ ይሁንታና ስምምነት የሥልጣን ዘመኑን ለአንድ ቀንም እንኳ ቢሆን ማራዘም የሚችልበት ምንም ዓይነት ሕጋዊ መሠረት ስለማይኖረው በዚህም ምክንያት ብዙ ቀውስ ወይም ትርምስ ስለሚፈጥር ይሄንን አለመረጋጋትና ቀውስ ለራሱ በሚመቸው መልኩ ለመቆጣጠር እንዲያመቸው ነው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አስቀድሞ ያወጀው!!!

አገዛዙ ምርጫው እንዲራዘም አጥብቆ የፈለገበት ምክንያት ከዚህ ቀደም ደጋግሜ እንደነገርኳቹህ ወያኔ/ኢሕአዴግ ለውጥ የሚል ድራማ አምጥቶ በአስደናቂ የትወና ብቃት እየተወነ እስከማጭበርበር ድረስ ሕዝብን በማወናበድ ወይም በማታለል የአገዛዝ ዘመኑን ለማራዘም የተገደደበት ምክንያት ለዘመናት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈለገውን ያህል የሰብአዊ መብት ጥሰትና ረገጣ ቢፈጽም በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ ተጠያቂ እንዳይሆንና የአጸፋ እርምጃ እንዳይወሰድበት ሲከላከሉለት የኖሩት ኋይት ሃውስን ተቆጣጥረውት የኖሩት ዲሞክራቶች ተሸንፈው ወይም ከኋይት ሃውስ ተጠራርገው ወጥተው መጽሐፍ ቅዱስ "ዮሴፍን የማያውቅ ንጉሥ መጣ!" እንደሚለው ኋይት ሃውስ ወያኔን በማያውቁትና በማይፈልጉት በትራምፐ አሥተዳደር በመያዙ እንደወትሮው ሁሉ የአሜሪካ መንግሥት ሊከላከልለትና ሊደግፈው ባለመቻሉ ነው!!!

ወያኔ/ኢሕአዴግ አሜሪካ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት አደጋ ላይ ስላለች ምናልባት ካልተራዘመ በስተቀር መስከረም ላይ በሚደረገው የአሜሪካ ምርጫ ጥብቅ ወዳጆቹና ቃልኪዳነኞቹ ዲሞክራቶች እነ ትራምፐን (ሪፐብሊካኖችን ማለት ስላልፈለኩ ነው) አሸንፈው ወደ ኋይት ሃውስ እንደሚመለሱ ተስፋ አድርጓል ወይም ያምናል፡፡ ዲሞክራቶች አሸንፈው ሥልጣን ከያዙ በኋላ እሱም የሚያደርገውን ምርጫ አጭበርብሮ "አሸነፍኩ!" ቢል እንደቀድሞው ሁሉ ስለሚከላከሉለትና ማንም እንዳይጠይቀው ወይም ተጽእኖ እንዳያደርስበት ስለሚያደርጉለት ነው የእኛ ምርጫ የአሜሪካ ምርጫ ከመደረጉ በፊት እንዲደረግ ያልፈለገውና ከአሜሪካ ምርጫ በኋላ እንዲደረግ ወይም እንዲራዘም የፈለገበት ምክንያት!!! ግልጽ ነው???

2ኛ. ይሄ በኮሮና ቫይረስ ሳቢያ የተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ለዚህ አገዛዝ ያመጣለት ሁለተኛው ያልታሰበ ሲሳይ ደግሞ ሕዝብ እንዲህ ከአደገኛው ዓለም አቀፍ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ለመጠበቅ በከፍተኛ

ጭንቀትና ሥጋት ተይዞ በየቤቱ ተከቶ ነፍሱን ለማዳን ጥረት በሚያደርግበት ወቅት ጨካኙና ፋሽስታዊው አገዛዝ ለሕዝብ ያሰበ መስሎ በመቅረብ በኮረና ቫይረስ አሳቦ የሕዝብን እንቅስቃሴንና ዝውውርን ከገደበና የአማራ ክልል የሚለውን ዙሪያውን ካጠረ በኋላ የተባበሩት መንግሥታት ሊቀመንበር አንቶኒዮ ጉተሬዥ የዓለምን ሕዝብ ከዚህ አደገኛ ወረርሽኝ ለመታደግ እንዲቻል ግጭት ውስጥ ያሉ የተለያዩ አካላት ሁሉ ሳይቀሩ የተኩስ አቁም አውጀው ወረርሽኙን በመከላከል ላይ እንዲያተኩሩ አጥብቀው አሳስበው እያለ ይሄ ኢሞራላዊው፣ ወንበዴውና ፋሽስቱ አገዛዝ ግን ወረርሽኙን እንደ ጥሩ ዕድልና አጋጣሚ በመጠቀም በፋኖ/አርበኞች ወይም በአማራ ገበሬ ላይ ያሻውን ግፍና እርምጃ ለመውሰድ ማስቻሉ ነው!!!

ገናም ገበሬውንም ትጥቅ ለማስፈታት ይጠቀምበታል፡፡ የአገዛዙ የዚህ ፀረ አማራ ዘመቻው ዓላማ ከፊታችን አገዛዙ በሚያመጣው የለየለት አንባገነናዊ ፈላጭ ቆራጭ የአገዛዝ ዘመን ምክንያት በሚከሰተው የፖለቲካ አለመረጋጋት አማራ አቅም ኖሮት የአገዛዙን ጭቆናና የፈላጭ ቆራጭ አንባገነናዊ ሥርዓት መቋቋም፣ መከላከል፣ መቃወም፣ መገዳደር፣ አሻፈረኝ ማለት እንዳይችል አድርጎ መስበር፣ አማራ ሙብቱን፣ ጥቅሙን፣ ነጻነቱን፣ ህልውናየን፣ ደኅንነቱን ሳይል ሰጥ ለበጥ ብሎ አንገቱን ሰብሮ የሚገዛ ባሪያ ሕዝብ እንዲሆን ማድረግ ነውና!!!

አገዛዙ ከቀናት በፊት በኮቪድ 19 ወረርሽኝ አሳቦ በፋኖ አርበኛ ላይ እርምጃ መውሰድ የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የአማራ ክልል የሚለውን ከእንቅስቃሴና ከዝውውር መገደቡን ማወጁ በፋኖ አርበኛ ላይ እርምጃ ለመውሰድ እንዲመቸው እንደሆነ እንዳይታወቅበት በማግስቱ ሌሎች ክልል የሚላቸውን የሀገሪቱ አካባቢዎችንም በተመሳሳይ ከእንቅስቃሴና ዝውውር መገደቡን ማወጁ ይታወሳል!!!

እናም ኢሞራላዊው፣ ወንበዴውና ፋሽስቱ አገዛዝ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ለእነዚህ ሁለት ዋና ዋና የውንብድና ተግባሮቹ ተጠቅሞበታል ወይም እየተጠቀመበት ይገኛል!!!

በል እንግዲህ ምስኪኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! መጭው ጊዜ ከወያኔ/ኢሕአዴግ ጋር ወይም በማወናበጃ ስሙ ከብልግና ፓርቲ ጋር እጅግ ጨለማ ነውና በማንኛውም ረገድ ወገብህን አጥብቀህ አስረህ እራስህን አዘጋጅ!!!

በተለይም ደግሞ ከአሁኑ እየጨፈጨፈህ ያለኸው የአማራ ሕዝብ ቁረጥ! ጨክንና ተነሥ!!! ትናንትና ላስታ ብልበላ ጊዮርጊስ አካባቢ ፋኖዎች ከፈጸሙት ሲበዛ የዋህነት የተሞላበት ስሕተት እራስህን አቅብ!!!

አገዛዙ አንተን ለመፍጀት ቆርጦ ሠራዊቱን አፍስሶ በዓይንህ በብረቱ እያየህ ድርድር ብሎ ሲጠራህ "እሺ!" ብሎ መሰብሰብ ምን ዓይነት የዋህነት ነው??? ይሄ አደገኛ ስሕተት ካስከፈለን ዋጋ በሌላ አካባቢ ያለኸው ፋኖ/አርበኛ ልትማር ይገባል!!!

አገዛዙ ስንት ወገኖቻችንን ነው በየጊዜው በዚህ 29 ዓመት ውስጥ ሽምግልና እያለ የሃይማኖት መሪዎችን ሳይቀር መስቀል አስይዞ እየላከ ደልሎ ካስገባ በኋላ እየጨፈጨፈ የፈጃቸው??? ሰው እንዴት ካሳለፈው አይማርም??? ሰው እንዴት ይሄንን ይረሳል???

እባክህን ወገን ሆይ! እንዲህ እያታለለ ሊፈጅህ ካልሆነ በስተቀር ይሄ የአጋንንት ጥርቅም አገዛዝ ሰላምና እርቅ የሚባል ነገር ፈጽሞ አይገባቸውምና አትጃጃሉ!!!

ትናንትና ሸምግለው ያስገቧቸውን ምን እንዳደረገ እያወቁ ዛሬም "ሸምግሉ!" እያለ መስቀል አሸክሞ ሲልካቸው እየተንተቱ የሚመጡና የሚያስቸግሩ ካህናት "እጅ ስጡና ይፍጃቹህ!" እያሉ ነውና አላርፍ ካሉ ቅጥረኞች ናቸውና ከጠላት ጋር እየደረብክ ግንባር ግንባሩን በለው!!!

ድል ለአማራ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው